ልባም ሴት ለመሆን ምን እናድርግ?

1.እግዚአብሔርንና መልካምነትን መፈለግ

- ከአርአያ እግዚአብሔር ወደ ወደ አምሳለ እግዚአብሔር (From Image to Likeness) ማደግ ነው::

  Image ⟹ Likeness

- ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት ነው፤ መንፈሳዊነት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ነው::

የቀጠለ...

2.መንፈሳዊነትን በሴትነት ማጎልበት

የኛ ዘመን ሰማእትነት

- ዘመናዊነት

Modernity is development **without dependency** –Ali mazuri, the Muse of modernity

- Justifying and normalizing sin…
- ሉላዊነት (Globalization)
- Secularism
- የተለያዩ ሚድያዎች ተፅዕኖ
- ፋሽን


የቀጠለ…

ከመኖር በላይ ያለ ማኖር
የፈጣሪ ጥበብ ድንቅ ቀመር
ለሴትነት የተሰጠ ክብር
ረቂቅ ፍጥረት ለአምላክ አምሳሉ
“አልቦ”ን ከ “ቦ” ማስታረቂያ ግብሩ!

- የሴት ማንነት ትውልድ የሚቀረፅበት በመሆኑ አለም ከትውልዱ አስቀድማ ሴቶችን እንደፍላጎቷ ለመቅረፅ እየታተረች ትገኛለች።


የቀጠለ…

Fig 2.2 First Children Conceived in Marriage



Source: Arnara Bachu, "Trends in Marital Status of U.S. Women at First Birth," U.S. Bureau of the Census Population Division Working Paper No. 20, March 1998

Fig. 4.4 Children Living with Never-Married Mother (in millions)



Source: Census Bureau, "Marital Status and Living Arrangements, March 1997"

የቀጠለ...

በ2003 በተደረገ ጥናት በመላው አለም 42 ሚሊዮን ውርጃ ተፈፅሟል፣ከ13–20% የእናቶች ሞት የሚከሰተው በዚሁ ሳቢያ ነው 90% የሚሆነው ፅንስ ማቋረጥ የሚከናወነው ባላደገት ሀገራት ነው::

አዲስአበባ በ598 ወጣቶች 2007 (2014) ጥናት

- 496 (82.9%) አርቶዶክሳውያን ናቸው::
- 521 (87.1%) ቤተ-ክርስቲያን እንሄዳለን ይላሉ
- 389 (66.6%) ልቅ የወሲብ ፊልም ያያሉ::
- **369 (61.7%) ሩካቤ ይፈጽማሉ::**
- ያረገዙ 50 (32%) ፤ውርጃ የፈጸሙ 44 (88%)

የቀጠለ...

መንፈሳዊነት ሂደት ነው ሊደረስበት እንደማይችል ሩቅ ተራራ አርቆ መመልከት አይገባም።

- **መሳ'ል**

የቀጠለ...

3. ምክንያተኝነትን ማራቅ

ወዳጄ “እኔ ይህን ማድረግ አልችልም” የምትል አትኹን፤ ባለ ኹለት ዲናሯ ሴት ትወቅሰሃለችና። ዳግመኛም “ወርቅም ብርም የለኝም” ብሎ የተናገረ ጴጥሮስ ይወቅሰሃልና።"ምናምንቴ ነኝ" አትበል፤ እንዲህ ስትል ምናምንቴዎቹ ሐዋርያት እንዳይሰሙህ! "እኔ በሽተኛ ነኝ" አትበል፤ በሽተኛው ጢሞቲዎስ ይታዘብሃልና። ፈጽመህ “እኔ ሌሎች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት አይሆንልኝም” አትበል። በእውነት ክርስቲያን ከኾንክ ይህን ከማድረግ ይልቅ አለማድረጉ ይከብዳልና። እግዚአብሔር እንዲህ እንድትኾን አድርጎ ፈጥሮሃልና ተፈጥሮህን መካድ አይቻልህም። ክርስቲያን በጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ ወንድሞቹ ብርሃኑን ከሚከለክል ይልቅ ፀሐይ ብርሃኗን ብትከለክል ይቀላልና። ስለዚህ አልጠቅምም አትበል እንደተባልን በቻልነው ሁሉ ቤተክርስቲያናችን የምትጠብቅብንን አገልግሎት መስጠት ይገባናል።

የቀጠለ...

4.ዕውቀትን መቀደስ

ምሳ 16፤22 “ገንዘብ ላደረገው ሰው እውቀት የሕይወት ምንጭ ነው፤ ስንፍና ግን የሰነፎች ቅጣት ነው”። “Knowledge is conversion matter into energy” ይላሉ ምሁራኑ እውቀትን ገንዘብ ማድረግ ለሕይወት ምንጭ ነው። ነገር ግን እውቀትን ሁሉ ማግበስበስ እንዳይገባ ቅዱስ አትናትዮስ ተግባራዊ ክርስትና ተብሎ በዲ/ን ሄኖክ ሀይሌ ተተርጉሞ በቀረበው መፅሐፋቸው “ራስህን ከአላስፈላጊ እውቀት ጠብቅ” ብለው አስቀምጠውልናል።

የቀጠለ...

5.በተሰጠን ፀጋ ለማገልገል መዘጋጀት

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በተግሳፁ **(ተግሳፅ ፫)፣ ምዕመናንን የማስተምርበት ሹመት ባገኝ ብሎ መመኘትን በሚከለክለው** አንቀፁ እንደተናገረ የተሰጠህ ላንተ የሚጠቅምህ ነውና ለምን ሌላውን ትሻለህ፣ ሌላ ፀጋ ስትመኝ እኮ እግዚአብሔር ለኔ የሰጠኝ የሚረባኝ አይደለም እያልክ እየከሰሰከው ነው፡፡ አንድ መክሊት የተሰጠውን ሰው ተመልከት ጌታውን መክሰስ ጀመረ፣ ጌታም ነቀፈው፡፡ እግዚአብሔር ካንተ በላይ ያውቅህል ምናልባት ፀጋው ቢሰጥህ ላትሰራበት ትችል ይሆናል ስለዚህ ወዳጄ መክሊትህን ቀብረኸዋልና አውጣው፡፡

የቀጠለ...

6.ቁርጠኝነት

“የሎጥን ሚስት አስቢት” ሉቃ. 17፡32

- ያለቆረጠ ሰው የትም መድረስ አይችልም።

የቀጠለ...

7.ሳራን መመልከት

ኢሳ51፡2 አባታችሁ አብርሃምን የወለዳቻድሁ ሳራንም አስቧት

ሳራን አስቧት ለምን አለ

1.አብርሃም እናትና አባቱን ትቶ ሲሰደድ አላገባህም አላለችም፣ከስጋ መለኪያ ይልቅ የልቦናው በልጦ ተቀብላዋለች

2.ውበት ደምግባቷ አሳብዩዋት ከእግዚአብሄር አልራቀችምና፡፡

ዘፍ

3.የዘመድ ፍቅር፣የቤተሰብ ናፍቆት እና የስጋ ህይወት አለኝታነትን አልተመካችም

ቅ.ቄርሎስ የዘመኑ ጋብቻ ራስና ምሳሌ ሳራ ናት፡፡

የቀጠለ...

4.እንግዳ መቀበሏ

5.መካንነቷ ቤቷን አላፈረሰውም።

የቀጠለ...

8.በምንዝር ጌጥ ራስን ከማስዋብ በላይ መልካምነትን ገንዘቧ ማድረግ

1ኛጢሞ2፡10 እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረት እና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ፣እግዚአብሄርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፣መልካም በማድረግ እንጂ በሹሩባና በወርቅ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ።።

- ማጌጥ ምንድን ነው?
- **ምሳ 11፡22 የወርቅ ቀለበት በእሪያ አፍንጫ እንደሆነ ከጥበብ የተለየች ቆንጆ ሴትም እንደዚያው ናት።።**



የቀጠለ...

አለባበስህ በጥንቃቄ ይሁን!ሃይ.አበው

ራዕ 16፤15 ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁእ ነው








ትውልድና ዘመን
ጉጥ



እንደ መቋጫ...

ምሳ 31፡10-31

10፤ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል

11፤የባልዋ ልብ ይታመንባታል፣ምርኮም አይጎድልባትም

12፤እድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች.ክፉም አታደርግም

13፤የበግ ጠጉርና የተልባ እግር ትፈልጋለእ፣በእጆችዋም ደስ ብልዋት ትሰራለእ

14፤እርስዋ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት፣ከሩቅ ሀገር ምግብዋን ትሰበስባለች

15፤ገና ሌሊት ሳለ ትነሳለች ለቤትዋም ሰዋች ምግባቸውን ለገረዶችም ተግባራቸውን ትሰጣለች

16፤እርሻንም ተመልክታ ትገዛለች፣ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች

17፤ወገብዋን በሀይል ትታጠቃለች፣ክንድዋንም ታበረታለች

የቀጠለ...

18፤ንግድዋ መልካም እንደሆነ ትመለከታለች፣መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም

19፤እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች፣ጣቶችዋም እንዝርት ይይዛሉ

20፤እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች ወደችግረኛም

21፤ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተነሳ አትፈራም፣የቤትዋ ሰዎች አጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና

22፤ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሰራለች፣ጥሩ በፍታና ቀይ ግጃ ትለብሳለች

23፤ባልዋ በአገር ሽማግሌዎች መካከል በሸንጎ በተቀመጠ ግዜ የታወቀ ይሆናል

24፤የበፍታ ቀሚስ እየሰራች ትሸጣለች፣ለነጋዴም ድግ ትሰጣለች፡፤

የቀጠለ...

25፤ብርታትና ከበሬታልብስዋ ነው፣በኃላም ዘመን ላይ ትስቃለች

26፤አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፣የርህራሄም ህግ በምላስዋ አለ

27፤የቤትዋንም ሰዎች አካሄድ በደህና ትመለከታለች፣የሀኬትንም እንጀራ አትበላም

28፤ልጆችዋ ይነሳሉ፣ምስጋናዋንም ይናገራሉ፣ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል

29፤መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፣አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ

30፤ውበት ሐሰት ነው፣ደምግባትም ከንቱ ነው፣እግዚአብሄርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች

31፤ከእጅዋ ፍሬ ስጡዋት፣ስራዎችዋም በሸንጎ ያመስግንዋት።።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!